# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች

# የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ




ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: M. Maillot
የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): E. Frischbutter; Sarah S.



ታሪክ 36 ከ 60 ዎቹ መሃከል

www.M1914.org

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*



ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።


አማርኛ

Amharic

ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ድንግል ወደ ሆነችው ማሪያም ወደምትባል አይሁዳዊት ሴት መልአኩ ገብርኤልን ላከው።



1

እንዲህ አላት “ድንግል ትፀንሻለሽ ወንድልጅም ትወልጃለሽ ሰሙንም እየሱስ ብለሽ ትጠሪዋለሽ፣ እሱም የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ለዘለዓለምም ይነግሣል።”



2


“ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?” በሚል
ይህች ሴት ጠየቀችው። “ከማንም ሰው
ጋር አልነበርኩም አላቸው” መልአኩም
ህፃኑ የመጣው ከእግዚአብር ዘንድ
ነው። ከሰው አባት የተገኘ
ልጅ አይደለም አላት።
3


መልአኩም ለማሪያም
እንዲህ አላት ዘመድሽ
ኤልሳቤጥም ፀንሳለች።
ይህ ተአምር ነው ብሎ
ማርያምም ዘመዷን
ኤልሣቤጥን ልትጎበኛት
ሄደች። ሁለቱም በጋራ
እግዚአብሔርን
አመሠገኑ።
4


ማሪያም ዮሴፍ ለሚባል
ሰው ታጭታ ነበር።
ማሪያምም እንደፀነሰች
በሰማ ጊዜ ዮሴፍም
በጣም አዘነ። ከሌላ
ሰው ልታረግዝ
እንደምትችልም
አሠበ።
5


መልአኩም በህልም ተገልጠለት ዮሴፍ
ሆይ ይህ ህፃን የተፀነሰው በሰው ፈቃድ
ሣይሆን በእግዚአብሔር ነውና ማሪያምን
ለመውሰድ አትፈራ አለው። ዮሴፍም
ማሪያም ይረዳት ነበር ህፃኑን
እንሱስንም ይንከባከበው ነበር።
6


ዮሴፍም እግዚአብሔርን አመነው ታዘዘውም
በተጨማሪም የሃገሪቱን ህግ
ይታዘዝና ለህጉም ይገዛለት
ነበር ምክንያቱም ...
7


... አዲስ ህግ ከመውጣቱ የተነሣ ማሪያና ዮሴፍ ሃገራቸውን
ለቅቀው ወደ ሌላ ሃገር ተሰደዱ
ቤተልሄምም በደረሱ ጊዜ
ታክስ (ግብር) ከፈሉ።
8


ማሪያም ልጅ የመውለጃዋ
ጊዜም ደረሠ ነገር ግን
ዮሴፍ የምትወልድበትን
ምቹ ቦታ ሊያገኝ አልቻለም
ሁሉም ክፍት
የሚመስሉ ቦታዎች
ሁሉ ሞልተው
ነበር፡፡
9


ዮሴፍም በመጨረሻው የከብቶች በረት አገኘ በዚያም
ህፃኑ እየሱስ ተወለደ። እናቱም ህፃኑን
በከብቶች በረት ውስጥ
አስተኛችው።
10


ይህ ሥፍራ የእንስሳት ማደሪያና መኖአቸው
የሚቀመጥበት ሥፍራ ነው።
11


በአቅራቢያው መንጋቸውን የሚያሠማሩ እረኞች ነበሩ
የእግዚአብሔር መልአክም ወደ እነርሱ ቀርቦ
ድንቅ ዜና የምሥራች
ነገራቸው።
12


ዛሬ በደዊት ከተማ አዳኝ የሆነው ክርስቶስ ኢየሱ ተወልዶላችኋል
ህፃኑም በከብቶች በረት በግርግም ተኝቶ
ታገኙታችሁ ብሎ ነገራቸው።
13


ወዲያው የሚያበሩ መልአክትም ተገልጠው
እግዚአብርሔን እንዲህ እያሉ ያመሰግኑት
ነበር ክብር በላይ ...
14


… በሠማይ በታችም በምድር ለእግዚአብሔር ይሁን ሰላምና በጎ ፈቃዱ በምድር ይሁን አሉ።
15
እረኞቹም እየሮጡ የተባለበት ሥፍራ ደረሱ ህፃኑንም ካዩት በኋላ ላገኙት ሰው ሁሉ መልአኩ ስለ ኢየሱስ (ስለህፃኑ) የነገራቸውን ሁሉ እውነት እንደሆነ መናገር ጀመሩ።
16
ከ40 ቀናትም በኋላ ማሪያምና ዮሴፍ ህፃኑን ወደ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ መልሠው አመጡት ስምኦን የሚባል ሰውም አገኙ እሱም ስለህፃኑ እግዚአብሔርን አመሠገነ ሌላው የእግዚአብሔር አገልጋይ ሃናንያ የሚባል ሰውም ለእግዚአብሔር ምሥጋናን አቀረበ።
17
ሁለቱም ኢየሱስ የእግዚአብር ልጅ እንደሆነ ያውቁ ነበር፣ ሊመጣ ያለው መሲህ ነው አሉ። ዮሴፍም 2 ወፎችን መሥዋዕት አደረገ። ይህም እግዚአብሔር ከሠጣቸው ህግ ውስጥ አንድ ሰው ልጅ ሲወልድ ማቅረብ ያለበት መሥዋት ነው።
18
ከጥቂት ጊዜያት በኋላም አንዲት ኮከብ ጠቢባንን እየመራች ህፃኑ ተወለደ ወደ ተባለበት ወደ ኢየሩሳሌም አደረሰቻቸው።
“የተወለደው የአይሁ ንጉሥ ወዴ አለ?” ሲሉ ጠየቁት “እሱንም ልናመልከው እንፈልጋን አሉ።”
19
እኝህ ጠቢባን ሠዎች ያሉትን ሁሉ ንጉሡ ሄሮዲስ ሰማ። እሱም ተረበሸና እየሱን መቼ እዳገኙት ጠየቃቸው “እኔም እሱን ላመልከው እፈልጋለሁ” አላቸው። ነገር ግን ውሸቱን ነበር ሊገድለው ይፈልግ ነበር።
20













የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

የማትዎስ ወንጌል ከምዕራፍ 1-2
እና የሉቃስ ወንጌል ከምዕራፍ 1-2

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣
ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን
ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ
ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ
አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ
በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ
ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ
አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር
በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር
ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ
እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16